የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፳፭
አዲስ አበባ ግንቦት ፴ ቀን ፲፱፻፺፰

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

12[th] Year No. 25
ADDIS ABABA 7[th] June, 2006


ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፬፻፺/፲፱፻፺፰ ዓ.ም

ለአሶሳ-ኩርሙክ መንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ... ገጽ ፫ሺ፬፻፲


CONTENTS


**Proclamation No. 490/2006**

Arab Bank for Economic Development in Africa Loan Agreement for financing the Assosa-Kurmuk Road Project Ratification Proclamation.... Page 3410


## አዋጅ ቁጥር ፬፻፺/፲፱፻፺፰

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለአሶሳ-ኩርሙክ መንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፮ሚሊዮን፭፻ሺህ የአሜሪካን ዶላር /ስድስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ የአሜሪካን ዶላር/ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል እ.ኤ.አ. ኖቬምበር ፲፮ ቀን ፪ሺ፭ ካርቱም የተፈረመ በመሆኑ፣

መሠረታዊ የኢኮኖሚ ዓለም ዐቀፍ ውሎች ተፈጻሚ ከመሆናቸው በፊት መፅደቅ ስላለባቸው፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለአሶሳ-ኩርሙክ መንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፬፻፺/፲፱፻፺፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## PROCLAMATION NO. 490/2006.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE ARAB BANK FOR ECONOMIC DEVELOPMENT IN AFRICA

**WHEREAS,** a Loan Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Arab Bank for Economic Development in Africa stipulating that the Arab Bank for Economic Development in Africa provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of six million five hundred thousand United States Dollars (USD 6,500,000) for financing the Assosa-Kurmuk Road Project was signed in Khartoum, on the 16[th] day of November 2005;

**WHEREAS,** basic Economic International agreements have to be ratified prior to entry into force;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 23[rd] day of May, 2006;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub-Article (1) and (12) of the Constitution it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Arab Bank for Economic Development in Africa Loan Agreement for financing the Assosa-Kurmuk Road Project Ratification Proclamation No.490/2006."


ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

**፪. የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል እ.ኤ.አ. ኖቬምበር ፲፮ ቀን ፪ሺ፭ ከርቱም የተፈረመው የብድር ስምምነት ፀድቋል።

**፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፮ሚሊዮን፭መቶሺህ የአሜሪካን ዶላር /ስድስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ የአሜሪካን ዶላር/ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

**፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ግንቦት ፴ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም.

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

**2. Ratification of the Agreement**

The Loan Agreement Signed between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Arab Bank for Economic Development in Africa on the 16th day of November 2005 is ratified.

**3. Power of the Minister of Finance and Economic Development**

The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of 6,500,000 USD (Six million five hundred thousand United States Dollars) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall enter in to force up on publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 7th day of June, 2006**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት